# አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**ANDINET NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (ANAASO)**

1334 9th Street, NW. Suite # 1 Washington DC. 20001.
Tel: (202) 462 0556 Fax: (202) 462 0557 Email: info@andinetusa.org

## ***የዛቻና ማስፈራራት ብዛት የህዝብን ትግል አያጓትተውም***

ህዝብ ለነፃነቱና ለመብቱ የሚያደርገው ተጋድሎ የተፈጥሮ ትግል ነው። በዓለማችን ታሪክ በአጠቃላይ፣ ማንኛውም ህብረተሰብ፣ በፈቃዱ ተገዢ ሆኖ አያውቅም፣ በጉልበት ልግዛህ ላለውም፣ በፍርሃት ወይም በአቅም ማነስ፣ ተንበርክኮ ፀጥ ለጥ ብሎ አልተገዛም። ሁሉም ህብረተሰብ፣ እንደ ማህበረሰቡና ወቅቱ ሁኔታ በተለያየ ስልት ጉልበተኛ ገዥዎችን ተቋቁሞ አስወግዷል። የባርነት ሥርዓት ከዓለማችን የተወገደው፣ በአሜሪካ የጥቁር ህዝብ ነፃነቱን የተጎናፀፈው፣ ሴቶች ከወንዶች ጋር ዕኩልነታቸውን ያረጋገጡት፣ ሀገሮች ከቅኝ አገዛዝ የተላቀቁት፣ በአጠቃላይ በገዥዎች በጎ ፈቃድ ሳይሆን፣ ከባድ መስዋዕትነትን ባስከፈለ ህዝባዊ ተጋድሎ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብም የነፃነት ተጋድሎ ታሪክ ከዚህ የተለየ አይደለም። ጣልያንን ጨምሮ የተለያዩ ሀገሮች ከሩቅም ከቅርብም የቃጡትን ወረራ፣ አኩሪ በሆነ የነፃነት ተጋድሎ መክቷል። በዚህም ትግሉ ምክንያት፣ ሀገራችን በቅኝ አገዛዝ ያልወደቀች ሀገርና የአፍሪቃ ጸረ-ቅኝ ግዛት ተጋድሎ ተምሳሌት እንድትሆን አድርጓታል። የአፄ ሀይለ ሥላሴን ንጉሳዊ አገዛዝና፣ የደርግን ወታደራዊ አገዛዝ፣ እምቢኝ አልገዛም በማለት፣ በሰው ሕይወትና በቁስ ወደር የሌለው መስዋዕትነት በመክፈል፣ ህዝባዊ የሆነ ታሪክ ሰርቷል።

በታሪክ አጋጣሚ አሁን የሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመፈናጠጥ ዕድሉ የገጠመው ገዢ መደብ፣ ደርግን ለመጣል ከተደረጉት ህዝባዊ ትግሎች ውስጥ አጋር ነበር። በዚህም ምክንያት፣ አንድ አንድ ወገኖች፣ ተስፋ አሳድረውበት ነበር። ትልቁ እንቆቅልሽ ግን፣ አቶ መለስ ዜናዊና በዙርያቸው የተሰባሰቡት፣ የተጋዳላይ ጓዶቻቸውን ዓላማ ወደጎን በመተው፣ የወንድምና እህቶቻቸውን ደም ደመ-ከልብ በማድረግ፣ በተለይም ደግሞ ከታሪክ ለመማር ባለመፍቀድ፣ ከቀድሞዎቹ ገዥዎች በባሰ መልኩ አምባገነን ለመሆን መብቃታቸው ነው።

እነመለስ የማሌሊት አቀንቃኝና የአልባንያ ሶሻሊዝም አራማጅ በመሆናቸው፣ የኮሙዩኒስት አይሉት የዲሞክራት፣ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚል ግራ የገባው ፖሊሲ ቀረጹ። ውጤቱም በኢትዮጵያ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ

ሁኔታዎች ቀውስ ሆነ። ሀሳብን መሰንዘር፤ መናገር መፃፍ፤ መደራጀት መሰብሰብ መቃወም፤ ማመን አለማመን የመሳሰሉት መሰረታዊ የሰው ልጆች የተፈጥሮ መብቶች በኢህአዴግ አገዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከለከሉ ሆኑ። በተቃራኒው፤ የሚያስከስሱ፤ የሚያሳስሩ፤ የሚያስሰድዱ እንዲሁም በጠራራ ፀሃይና በጨለማ የሚያስገድሉ ሆኑ።

እሥራቱ፤ መሰደዱ፤ መገደሉ እንዳለ ሆኖ፤ ተፈጥሮ ነውና፤ ኢትዮጵያዊው ግን የነፃነትና የመብት ተጋድሎዉን አላቋረጠም። በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም እልህ አስጨራሹን ትግል ተያይዞታል። በተለይ በሀገር ቤት በሚደረገው ትግል፤ የአንድነት ፓርቲ ከቅንጅት የወረሰውን የህዝብ አደራ በሚገባ በመወጣት ላይ ይገኛል። ከገዥው መደብ የሚደረደሩትን ተልካሻ ምክንያቶች በማለፍ፤ የደበዘዘ የመሰለውን ትግል አንድ ምዕራፍ ወደፊት ይዞት ሂዷል። ይህ ሁኔታ በገዥው መደብ በበጎ ሊታይ እንደማይችል የተጠበቀ በመሆኑ፤ አዲስ ደንቃራ ይዞ መቅረቡ አስገራሚ አይደለም።

የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ላይ አዲስ ጥቃት ይዞ ብቅ አለ። የቀድሞው ቅንጅት ፓርቲ አመራሮች ከእስር ቤት ሲወጡ፤ በሀገር ሽማግሌዎች ጣልቃ ገብነት፤ በተካሄደ የፖለቲክ ድርድር፤ የድርድሩም ውጤት በፈጠረው ስምምነተ ለመሆኑ፤ ሀገር የሚያውቀው ፀሃይ የሞቀው ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ፤ የፖለቲካ አክሮባት በመጫወት የሰለጠነው ገዥው ፓርቲ፤ ወ/ት ብርቱካንን አቋምሽን አስተባብይ ያለበለዛ ዋ የሚል ዛቻ አስተላልፏል።

ይህ የሚያመላክተው፤ አንድነት ፓርቲ የቀየሰው ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ገዥውን መደብ ከጠበቀው በላይ እያስፈሩት እንደሆነ ነው። ትግሉ እየገፋና እየጠነከረ ሲሄድ ገዥው ፓርቲ ፈራ። የኢትዮጵያ ህዝብ ገገርውን ፓርቲ በማያውቀው የሰላማዊ ትግል ማናገር ሲጀምር፤ ገዥው ፓርቲ ወደ ሚያውቀው ቋንቋ፤ የሀይልና ጉልበት አገዛዝ አመራ። ገዥው ፓርቲ ጠንቅቆ እንዲረዳው የምንፈልገው ግን፤ አንድነት የህጋዊና ሰላማዊ ትግሉን ርዝመት፤ ውርደትና ጥለቀት በሚገባ እንደሚያውቀው፤ ለመስዋዕትነቱም ፍፁም ዝግጁ እንደሆነ ነው። በተለይም መሪዎቻችን በግንባር በመሆን፤ ያቺ የነፃነት ቀን በኢትዮጵያ እስክትሰፍን ድረስ፤ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውም አደጋ፤ በቆራጥነት ለመጋፈጥ ዝግጁ ናቸው።

በሀገር ውስጥም በውጭ ሀገርም የምትገኙ የአንድነት ፓርቲ አባለትና ደጋፊዎች ሁሉ፤ በአጠቃላይ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ የገዥውን መደብ አዲስ ስልት በውል በማጤን በወ/ት ብርቱካን በግል በአንድነት ፓርቲ ላይና በሰፊው ህዝብ የነፃነት ተጋድሎ የተቃጣውን ጥቃት መቋቋም ይኖርበታል።

የቀድሞው ቅንጅት አመራር አባላት የነበራችሁና፤ በገዥው መደብ አሳዛኝ የፈጠራ “ሀገር መካድና ዘር የማጥፋት” ወንጀል ተከሳቹህ ዕድሜ ይፍታህ ተፈርዶባቹህ የነበራቹህ በአጠቃላይ፤ በአሁኑ ወቅት በሀገር ቤትም ይሁን ከሀገር ውጭ የምትገኙ፤ ከቀድሞው የእስር ጓዳቹህ ጋር የመቆም የሞራል ግዴታ ስላለባቹህ፤ ከእስር ቤት የተፈታቹህበትን አግባብ ለህዝብ ይፋ በማድረግ፤ ገዥውን መደብ እንድታጋልጡ ጥሪ እናቀርባለን።

በራሳቸሁ ተነሳሽነት፣ በሀገር ሽማግሌነት በመደራጀት፣ በቀድሞው የቅንጅት እስረኞችና በገዥው መደብ መሀከል የማደራደር ሃላፊነትን የወሰዳቹህ ግለሰቦች፣ በቅድሚያ ለተነሳሽነታቹህና ላበረከታችሁት አስተዋፅኦ ምስጋናችንን እያቀረብን፣ አሁን ገዥው ፓርቲ በወ/ት ብርቱካን ላይ የፈጠረው ጫና፣ ሊፈጥረው የሚችለውን ሁኔታ ከወዲሁ በመረዳት፣ ከእስር ቤት የተለቀቁበትን አግባብ ለህዝብ ይፋ እንድታደርጉ አጥብቀን እንጠይቃቹሃለን። ከምንም በላይ ለህሊናቹህና ለእምላካቹህ የምታድሩ መሆናችሁን በመተማመን፣ አፋጣኝ የሆነ ተግባራዊ ምላሻቹህን እንጠብቃለን።

በመጨረሻም፣ ሀገር ቤት የሚገኘው የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት፣ ሁሉም ለአንዱ፣ አንዱ ለሁሉም በሚለው መርህ መሰረት፣ በሊቀመንበራችን ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ በግል፣ በአጠቃላይም በአንድነት ፓርቲ ላይ የተቃጣውን ጥቃት፣ እስከ ዛሬ እንዳደረጋችሁት ሁሉ፣ በአንድነት በመቆም፣ በበሳል አመራር፣ እንደምታስወግዱትና፣ ህዝቡን እንደምትመሩ፣ ትግሉንም ወደፊት እንደምታራምዱ ምንም ጥርጥ የለንም።

እኛም በአሜሪካና በካናዳ የምንገኝ የአንድነት ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበራት አመራርና አባላት በአጠቃላይ፣ አንድነት ፓርቲ ይዞ የተነሳቸውን የዲሞክራሲና ፍትህ ፅንሰ-ሀሳቦች፣ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ ህዝባዊ ትግል፣ ከምንጊዜውም በበለጠ በመደራጀት ለማቀጣጠል ከወዲሁ ህዝባዊ ቃል እንገባለን። በተለይም በወቅቱ በተፈጠረው ችግር፣ ከወ/ት ብርቱካን ጎን ሙሉ በሙሉ መቆማችንን እናረጋግጣለን፡፡

## የዛቻና ማስፈራራት ብዛት የህዝብን ትግል አያጓትተውም !!!